# ይድረስ ለአቶ ጌታቸው ረዳ!

ከአደራ ቃል

ወደ ዋናው ቁመነገር ከመግባቴ በፊት አንድ አንተን አስመልክቶ ከሚከነክኑኝና ለአንተ የነበረኝን ከበሬታ በጣም ዝቅ ከአረጉት ነገሮች ውስጥ አንዱ ስለ ትግርይ ሕዝብ ያልኸው ነበር። ለትግርይ ሕዝብ በአንደኛ ደረጃ ጠላትኅ ማነው ተብሎ ሲጠየቅ አማራ ነው አለ በሚል ያቀረብኸው ሰርቬ ብጤ ጹሁፍ ነው። የሚያልፍ ቀን የማያልፍ ሥም ይሰጣል እንዲሉ እንደ ጧት ጤዛ ረግፎ ለሚቀረው ሕይወትህ፣ አጉል ዝናና ርካሽ ስም ለማትረፍ ብለኅ ኅሊናኅን ለቀብድ፣ የትግራይን ሕዝብ ለገበያ ማውጣትኅ በጣም ያሳዝናል! ቀድሞ ነገር አንድ ኅሊና ካለው ግለሰብ ያውም ተማርሁ ከሚል ሰው እንደዚኅ አይነት ፀያፍ ጹህፍ ሊቀርብ አይገባውም ነበር። አለመታደል ሆነና ለትግራይ ሕዝብ ልትከራከርለት፣ ልትመሠክርለትና ልታከብረው ሲገባህ፣ አንተም እንደ ሌሎቹ የትግራይን ሕዝብ በነቂስ ከወያኔ ጋር ደብልቀህ የጭቃ ጅራፍኅን አጮህበት። ታዲያ ካላጣኸው ሥም ሁሉ የትግራይን ሕዝብ በነቂስ ወያኔ ብለኅ መሰየምህ ለትግራይ ሕዝብ ሥድብ አይደለም ብለኅ ታምናለኅ? እንዲያው ውነት ተብሎ ቢገመት እንኳን በዕንደዚህ አይነት አሉታዊ እንደምታ ተጠያቂው ወያኔ ነው ብሎ ወያኔን ከምላዓቱ ለመነጠልና ጥግ ለማስያዝ መጣር አለብን እንጅ ሁሉም የትግራይ ሕዝብ ተጠያቂ ነው በሚል ፈሊጥ ለወያኔ መጥቀም ጥሩ ሊሆን አይችልም እልሃለሁ።

በተቃራኒው ግን የትግራይ ሕዝብ መንፈስ መለካት ያለበት በነአሉላ አባነጋ፣ በነ ተስፋዬ ደበሳይ፣ በነ ጋይም ገብረሥላሴና በዕናት ድርጅታቸው ኢ ሕ አ ፓ ጥላ ሥር ተሰባስበው ለኢትዮጵያ አንድነትና ልዑላዊነት በታገሉት የቁርጥ ቀን ልጆቹ ነው እንጂ በባንዳው መለስ ዜናዊ፣ በነ ኅሊና ቢሱ ሰብሃት ነጋና በወያኔ መንጋ መንፈስ ሊሆን ከቶ አይችልም እልሃለሁ። አየህ እዚኅ ላይ እኔና አንተ በአለን ማነጣጠሪያ ነጥብ [point of reference] ተለያየን:: እኔ የትግራይ ሕዝብ መንፈስ መለካት ያለበት በጋራ ጀግኖቻችን መንፈስ ነው ስል፣ አንተ ደግሞ የትግራይን ሕዝብ እንዳለ በወያኔ ሚዛን ውስጥ አስገብተኅ አቀለልኸው። መንፈሱንም አውርደኅ፣ሸረህና አኮላሽተህ ወያኔ አደረግኸው።፡

ለኔ ወያኔ ሁሉ ትግሬ ነው የሚለውአውሬውን ወያኔን በሚገባ ሲገልጽ ትግሬ ሁሉ ወያኔ ነው የሚለው ግን በጣም መደዴና የጅምላ ጨኸት ነው ዕልሃለሁ። ሌላው አቶ ጌታቼው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወያኔ ጋር ግብግብ በገጠመበት፣ የአንድነት ኃይሎች ሁሉ ተባብረው ይደርሱለት ዘንድም ሕዝቡ በጉጉት በሚጠብቅበት በዚኅ ወሳኝ ወቅትና ወያኔ ሊውድቅ አንድ ቀን ጀንበር ሲቀረው በኢ ሕ አ ፓ ላይ መዝመትኅ ምን ይባላል? ዛሬ አማራውን እያፈናቀለው፣ ለዘር እንዳይተርፍ የሚያመክን መርፌ እየወጋው ያለው፣ ለም መሬቱን ቀምቶ ለትግራይ እየሰጠበት ያለው ወያኔ እንጂ ኢ ሕ አ ፓ እኮ አይደለም። ታዲያ ወያኔን ትቶ በኢሕ አ ፓ ላይ መጮህ ምን ይባላል? ሌላ ትርጉም እስካልተሰጠው ድረስ የአንድነት ኃይል ስንል እኮ ኢ ሕ አ ፓ እና አማራ ቁልፍ ሚና ካሚጫወቱት ወገኖች ውስጥ የመጀመሪያቹ ናቸው።

ናቸውናም በአማራና በኢ ሕ አ ፓ መካከል ልዩነት ለመፍጠር መጣር የወያኔና ግብረአበሮቹ ስልት፣ ጥረትና ዘዴ መሆኑም አገር ያወቀው ፀሃይ የሞቀው ሃቅ ነው። በአጭሩ አሁን ሁሉም ነገር ወደ ጦር ግንባር ሁሉም ነገር ወደ ወያኔ በተባለበትና ድርጅቱም ያለ የሌለ ኃይሉን በወያኔ ላይ ባነጣጠረበት ወቅት በ ኢ ሕ አ ፓ ላይ መዝመትኅ ሰልፍህ ከማን መሆኑን ያሳያል ማለት ነው። ፈርዶበት አማራ! አለ ገጣሚው አሊ ሁሴን- ተወካዩ በረከት  ስምን፣ ከሳሹ ተስፋየ ገብረአብና፣ ጠበቃው ጌታቼው ረዳ ሁነው ሲሰየሙበት በማየቱ እኮ ነው።

ዕውነትም ፈርዶበት አማራ! አቶ ጌታቼው እንዲያው በፈጠረኅ ዓምላክ ዳኛውም፣ እናንተ፣ ጠበቃውም እናንተ፣ ከሳሹም እናንተ፣ መስካሪውም እናንተ በሆናችሁበት ፍርድቤት እንዴት ብለን ነው እኛ ፍርድልናገኝ የምንችለው? በአጭሩ አማራና ኢ ሕ አ ፓ በናንተ ፍርድ ቤት ፍትህም አይጠብቁም ብየህ አልፋለሁ።

አቶ ጌታቼው እኛ ኢትዮጵያውያን አረመኔዎች አይደለንም። ፍርሃ-ዕግዚያብሄር ያለን ሕዝቦች፣ ሰውን ያኅል ፍጡር አይደለም የጋማ ከብት የማንበላ መሆናችንን እኛ አይደለንም ዓለም በሙሉ ግጥም አርጎ የሚያውቀው እውነታ ነው። ጉምዝ

አማራ በላ ብለን ከብጤዎችህ ጋር ሁነህ በርካታ ግብዞችን ስታታልል አይተን ሰምተን ዝም አላልነም። ይህች የወያኔ የዕጅ ሥራ ናት ወገን ተጠንቀቅ ነው ያልነው። ነውናም ጉምዝ አማራ በላ ብሎ ጉምዝን በአረመኔነት መክሰስ ዘረኝነት አይደለም ትለኛለኅ? ታዲያ ዘረኝነትና ወያኔነት እኮ ተወራራሽ ናቸው። ናቸውናም የወያኔን ፖለቲካ ነው የምታራምደው ማለት ነው። አማራን ከጉምዙ፣ ከኦሮሞው፣ ከቅማንቱ፣ ከአገው ወዘተ ነጥሎ ለመምታት ወያኔ አዘውትሮ የሚጠቀምበትን ዘዴ አበክረን ስለምናውቅ ያኔ ነው የአንተ ነገር የገባን። ዘር ከልጓም ይስባል አይደል፣ በዕናንተ ደግሞ ይህ አዲስ ነገር አይደለም። ወያኔን ማመን ቀብሮ ነው የምንለውም ለዚያ ነው። ወያኔ ባፍ-ጢሙ ሊደፋ ሲል በ፩፩ኛው ስዓት መምጣትህና በኢ ሕ አ ፓ ላይ መዝመትኅም እንዲያው በድንገት፣ እንዲሁ በአጋጣሚ ሊሆን እንድማይችልም ሆድኅ ያውቀዋል።

አቶ ጌታቼው ሰሞኑን ደግሞ ትግራይ ውስጥ ታስረህ እንደነበርና አንድ ከኢ ሕ አ ፓ የመጣ ጀሌ ሲያስቃይህ ሌላው የደርግ ካድሬ እንደተማለደህ ጽፈሃል። ወይ ቅሌት! በነገራችን ላይ አንተ ትግራይ ወስጥ ታሰርሁ ባልህበት ጊዜ በመንግሥቱ ኃይለማሪያም ይመራ የነበረው ሰደድ የመኢሶንን፣ የኢጫሐትን፣ የማሌሬድንና፣ የወዝሊግን ነብሰ-ገዳይ ካድሬዎችን በጅምላ ያሰረበት ዘመን መሆኑ ሁላችንም የምናውቀው ታሪክ ነው። ታዲያ በሻቢያ፣ ወይንም በወያኔ፣ ወይንም በ ኢ ሕ አ ፓ ተጠርጥረህ ካልተያዝህ በምን ነበር የተያዝኸው? የዛሬውን አያርገውና ገና ሳትቀየር ሻቢያዎቹና ወያኔዎቹ ከድሮ ጀምሮ፣ ገና እዚህ ሀገር ዕንደመጣኅ እኮ ነው ያራቁህ ለምን ነበር? መቼም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የአማራ ጠበቃ ነኝ ስላልሀቸው ወይንም ጠባቦች ናችሁ ተገንጣይ ናችሁ ብለኅ አቋም በመውሰድኅ እንዳልሆነ ሁላችንም የምናውቀው ሃቅ ነው። ዛሬም ሁሉም በህይወወት ስላሉ ምስክሮች ናቸው።

ወያኔና ሻቢያ ለምስክርነት ባትበቁም ቅሉ። ይኅን አስመልክቶም ብዙ ነገር ገና ማጠናቀርና አንተን በሚገባና በሚገባኅ ቋንቋ ማጋለጥ የግድ ይሆናል ማለት ነው። ገና ስንመጣ ግን መኢሶኖች ለብቻቸው ከኢ ሕ አ ፓዎች ተነጥለው ራቅ ብለው ማለት ነው ለብቻቸው መኖራቸው በሌላ ሳይሆን በፖለቲካ መስመር ልዩነት ስለነበረንና ስላለን ነው። ታዲያ ለምን ይሆን እነርሱን መርጠህ፣ እኛን ዘግተህ ከነርሱ ጋር አብረኅ ስትኖር የነበር? በዚያን ጊዜ መኢሶኖቹ ከደቡብ ኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የመጡት በጅቡቲ በኩል ነበር። አንተ ግን በሱዳን ነው የመጣሃው።
ግን እነርሱን ስታገኝ ወገኖችኅንና እኛን ርቀኅ ተቀላቀልሃቼው። ለምን? እንኛንም ሆነ ዘመዶችኅን ለዕግዚያብሄር ሰላምታ እንኳ ነስተህ አንገትህን ደፍተህ ስታልፈን የነበረው ለምንደን ነው? ሁላችንም በህይወት አለን። በሌላ በኩል ደግሞ በጅቡቲም ገቡ በሱዳን ኢ ሕ አ ፓዎች በአንድ ላይ ሲኖሩ እናንተ ደግሞ ተፈላልጋችሁ አብራችሁ መኖታችሁ በሌላ ሳይሆን በፖለቲካ ግንኙነታችሁ ብቻ መሆኑን ማን ሊያጣው ይችላል። እንደተኮነነች ነብስ ከብዙሃኑ ተነጥላችሁ ሦስት ሁናችሁ ስትኖሩ፣ ከሦስታችሁ አንዱ በተኛበት ሞቶ ለሃዘን ስንመጣ ጋቢ ለብሰኅ እኛ ስንገባ እንዴት እንደተሸማቀቅኅ ሁሉ ትዝ ይለናል። ይኸን ሁሉ ነገር አሁን ያመጣሁት በኢ ሕ አ ፓዎች ላይ ያለኅ ጥላቻ ስር የሰደደ መሆኑን ለሌሎች ካልሆነ በስተቀር ዕዚኅ ለምንኖረውና ለብዙ ጊዜ ለምናውቅኅ አዲስ አይደለም ለማለት ነው። ወደ ኋላ ግን በወያኔ ላይ አቋም አለኝ ስላልኅ ኢ ሕ አ ፓና መኢሶንም በኢድህቅ ሲሰሩ ነበርና መጀመሪያ የአገር ጉዳይ በሚል አንተን አለመግፋቱ ጥሩ ነው በሚል ነበር የተውንኅ። አልፎ ተርፎም እናበረታታው ወያኔዎችና ሻቢያዎች ለብቻው እንዳያጠቁት በሚል ዘመድ አረግነኅ።
የአለአቻ ጋብቻው ጉድኅ እንዳለ ሁኖ ማለቴ ነው።

ይሄ ሁሉ ሲሆን ግን አንድም ቀን ለስብሰባ ስትመጣ ወይንም በዕለቱ ኢ ድ ኃ ቅን ወደኋላም ህብረቱን ሲቋቋም በኮሚቴ አባልነትም ሆነ ሌላ ደርጃ ተሳትፈኅ አታውቅም።፡ የሃሳብ፣ የሞራል፣ የቁሳቁስም ሆነ የገንዘብ አስተዋጾ አድርገኅ አታውቅም። አገር መውደድ ማለት ባንዲራ ትከሻ ላይ ለጥፎ ራስን pose ማድረግ ማለት አይደለም። ወይንም ደስና ሞቅ ባለኅ ቁጥር በሚታገሉ ኢትዮጵያውያን ላይ የማያባራ አሉባልታ ማሠራጨት አይደለም።

አቶ ጌታቼው አገር ወዳድ ማለት በተጨባጭ አገርንና ሕዝብን በሚበጁ ልዩ ልዩ በሆኑ ፖለቲካዊ፣ ማህበረሰባዊና እኮኖሚያዊ እንቅሥቃሴዎች ላይ መሳተፍን ይጠቃል። ኢ ሕ አ ፓዎች ለምሳሌ አንደኛ በአለህበት ከተማና ስቴት ሳይቀር፣ በአጠቃላይ በአሜሪካና በካናዳ ውስጥ የተቋቋሙ የሃይማኖት ተቋማትን፣ ዕድሮችና ልዩ ልዩ ሕዝባዊ ኮሚኒቲዎችንና የንግድ ተቋማትን ሁሉ በማቋቋም ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። ሁለተኛ ዛሬ ኢትዮጵያዊያኖችን በየዓመቱ በማገናኜት ረገድ አንቱ የተባለውን የኢትዮጵያዊያኖችን የዕግር ኳስ ፌደሬሽ በማቋቋምና በማደራጀት ከፍተኛውን ሚና ተጫውተዋል። ሦስተኛ አንድ አይደለም፣ ሁለት አይደለም ከ 15 በላይ የሚሆኑ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችን ወደ አንድ በማምጣት ብቻ አይደለም ከሰሜን አሜሪካ እስከ ኦሻና፣ ከአኡስትራሊያ፣ ከኢሮፐ፣ ከምሥራቅ አፍሪካና ኢትዮጵያ ሳይቀር ደጋፊ

ኮሚቴዎችን በማዋቀር ኢድኃን ያቋቋሙና የታገሉ ኢ. ሕ አ ፓዎችና አገር ወዳዶች ናቸው። አንተ ምን አደረግህ?፡ እነርሱን አሉታዊ በሆነ መልክ ከመክሠሥና ከማብጠልጠል ባሻገር? በነገራችን ላይ በአለንበት አካባቢ ስብሰባም ሆነ ራት ግብዣ ላይ ከእንግዶች ጋርና ከኮሚቴ አባላት ጋር ራት ስትበላ አይቼኅ አላውቅም። በኅይወቴ ያየሁህ አረጋዊ በርሄ የራሱን ዘሮች ለመገናኘት በመጣበት ጊዜና ኢርትራና ኢትዮጵያ በሚል የወያኔ ቅጥረኞች በአዘጋጁት ስብሰባ እነ ጃዋርና ሌሎችን ስም አልጠቅስም በመጡበት ጊዜ ብቻ ነው፤ ለምን ይሆን?

ሌላው አቶ ጌታቼው ኢ. ሕ አ ፓንና አባላቱን አስመልክቶ ከልት ከልት የሚል ነገር ታበዛለኅ። ኸረ ለመሆኑ ከልት ማለት ምን ማለት ነው? መቼም ኢ. ሕ አ ፓዎች በአንድ የተወሰነ ምስል ወይም ነገር ወይንም ግለሰብ የሚያመልኩ ጣኦት ጠራቢዎች አለመሆናቼውን ድፍን ኢትዮጵያ ያዉቀዋል። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ተክለሰውትን መገንባትና በግለሰቦች የማምለክን አደጋ የተዋጋና በምትኩም በጋራ አመራርና ውሳኔ የሚያምንና የሚመራ ድርጅት ኢ. ሕ አ ፓ ብቻ ነው። የጋራ አመራርና የጋራ ውሳኔ በጽንሰ ሃሳብ፣ በንደፈ-ሃሳብና በአፈጻጸም ረገድም ተግባራዊ ያደረገ ድርጅት ቢኖር ኢ. ሕ አ ፓ ነው እልሃለሁ። ሌላስ፣ ኢ. ሕ አ ፓዎች ሰማይ አይታረስ ንጉስ አይከሰስ ወስዩመ እግዚያብሄር በሚባልበት ዘመን መንግሥት የሕዝብ እንጂ ምርጥ ነን የሚሉ ግለሰቦች መፈንጫ አይደለም በማለት ድቅድቁን ጨለማ ሰብረው የወጡ አንጸባራቂ ከዋክብቶች ናቸው። ለመሆኑ አንተ የት ነው የምትኖረው? ኢ. ሕ አ ፓዎች መንግሥት የሕዝብ እንጂ የምርጦች አይደለም ሲሉ ደጉ ንጉሳችን ይኑር ለክብራችን ከሚሉ ጥገኛና ባለጸጋ አምላኪዎች ይለያሉ ማለት ነው እኮ። አንተ የትኛው ነህ? ከልቱ ነሕ ወይስ ገልቱ? ከልት ስንል ከልት ሲሉ! ከጥራዝ ነጠቆች ጋር ልዩነታችን ዕትየለሌ ነው እልሃለሁ። በአጭሩ የኢ. ሕ አ ፓዎች እምነት፣ አላማና ጽናታቸው በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ዙሪያ እንጂ በመለስና በመንግሥቱ ዙሪያ አይደለም። በግለ-ሰቦች ተከለ ሰውነት ዙሪያም አይደለም። በዓላማ ዙሪያ ነው። አላማቸውም እንደዘመዶችህ በጓሮ ፖለቲካ ሳይሆን፣ በዘረኝነት ሳይሆን፣ በብሄራዊ አንድነት፣ ዕኩልነትን መሠረት ባደረገ አንድነት፣ በዴሞክራሲና በሕዝባዊ ልዑላዊነት ዙሪያ ያጠነጠነ ኢትዮጵያዊነት ነው። በዓላማና በተክለ-ሰውነት መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነትለይተህ አለማወቅህ ደግሞ ያው አቅምኅንና ማንነትኅን ፍንትው አድርጎ ያሳያል። አንተ እንደምትቀባጥረው ቢሆንማ ኑሮ እነ ብርሃነ መስቀል ሲከዱ ድርጅቱ በፈረሰ ነበር። እነ መርሻ ዮሴፍ ሲደገሙም መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ ብለው ትግላጨውን ቀጠሉ እንጂ አልፈረሱም ዕልሃለሁ።

ኢ. ሕ አ ፓዎች ታጋይ ይሞታል ትግል አይሞትም ብለው በዓላማ ዙሪያ በመሰባሰባቸው ዛሬ በዙም አነሱም አለና ብለው በጽናት ቁመው በህይወት አሉ። ከብዛት ጥራት ነውና ቢቀጥኑም ጠጅናቸው! አለና የሚለው ሥነ-ቃል ቋሚና መሪ ቃላቸው ሁኖ ትግላቸውን ቀጥለዋል ማለት ነው። አንተ የባጥ የቆጡን ስትቀባጥር እነርሱ ትግል ላይ ናቸው ማለቴም ነው። እንደ አንተና መሰሎችኅ እንደ ፈሳ ዝንጀሮ ከመንጋው ተነጥለው በብርድና በቁር መሰቃየት ግን ሲያልፍም አይነካቸውም ማለቴም ነው። ኢ. ህ አ ፓዎች እንደደርግ ካድሬዎች በደመወዝ ተቀጥረው ነብስ ያጠፉበትና በሥልጣን ዙሪያ ያሚረቱበት ዘመን ስሌለ በሕዝብ ፊት ጥሩ የሆነ ከብር፣ ፍቅርና ግርማ አላቸው። ስለሆነም የሕዝብ ደም በዕጃቸው ይዘው አይዞሩም።፡ ንጹህ ህሊና አላቸው፣ በመሆናቸውም በሰላም ከሕዝባቸው ጋር እፎይ ብለው ይኖራሉ! ከወያኔም ጋር ሆነ ከደርግ ጋር ሥልጣን ሲጋሩ ግን ታይተውም፣ ተሰምተውም አያዉቁ። ታዲያ ለሥልጣን የቋመጡ የምትለዋ ቃላትኅ ከምን የመጣች ነች?፡ ያው እንዳመልህ ቆርጦ መለጠፍና ቃላትን ደርድሮ አንባቢን confuse ለማድረግ ከሆነ ይመችኅ ደርድረው። ግን ዕኔ አንተን ብሆን ከሆንሁ ደግሞ ትርፉ ቅሌት በመሆኑ ምኞቴን ሽሬዋለሁ ይቅርታ! ስለዚህ ትርጉሙ ለራሴ፣ መልዕክቱም ለምንትሴ ብለህ በድርቡ ቃላቱን ሰርዘው። ለሥልጣን የቋመጡ የምትለዋን ማለቴ ነው። ቅሌትና ውርደት ወግና ማረጌ ነው ካልኅ ደግሞ ታጥቀኸው ዙር። የቃላት ግድፈት ሳይሆን የቋንቋ ዕጥረት ከሆነ ደግሞ ከመጠምጠም መማሩ ይቅደም ነውና ብትማር ይሻልሃል።፡ ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮሃል እንደሚባለው በሞቅውህና በተናደድህ ቁጥር በኢ. ሕ አ ፓዎች ላይ መጮህን አቁም። ሌላው አቶ ጌታቼው፣ ኢ. ሕ አ ፓዎችን ድርጅታቸውን ይወዳሉ በሚል አሉታዊ መንፈስ ትከሳቸዋለህ። ድርጅት እኮ መሳሪያ ነው። ድር ቢያብር አንበሳ ያሥር የሚለው ብሂል እኮ የመደራጀትን ጠቀሜታ በግልጽም ሆነ በዉስጠ-ወይራው አሥሮ የያዘ አባባልነው።

networking የሚባለው ነው! በርግጥ በተፈጥሯቸው ከሰው ጋር አብሮ መኖር የማይችሉ፣ ራሳቸውን ለሕግ፣ ለሕብረተሰቡ የጋራ ዕሴቶችና ለህሌናቸው የማይገዙ፣ ዲስፕሊን የሌላቸው ከራሳቸው በስተቀር ለሌላው ግድ የሌላቸው ስግብግብና ራስ ወዳድ ግለሰቦች እንደ ኢ. ሕ አ ፓ ዎች በድርጅት ታቅፈው ድርጅታዊና ሕዝባዊ ሥራን እንዲሰሩ አይጠበቅም። ይህን አይነት ጸጋ፣ ችሎታና ትዕግሥት ያላቸው ኢ. ሕ አ ፓዎች እውቀታቸውንና ጥበባቸውን በጊዜ ተጠቅመው ሕዝብና አገራቸውን ለማገልገል ሁሌም ዝግጁ ናቸው። ትግሥቱንም፣ እውቀቱንም፣ ጥበብና ብልሃቱን

የነሳቸውና የሌላቸው ግለሰቦች ደግሞ በድርጅት ተሰባስበው በጋራ መሥራት ስለማይችሉ እነደተኮነነች ነብስ ከሕብረተሰቡ ተነጥለው የብችኝነት ኑሯቸውን ይገፋሉ ማለት ነው።

ሌላው በኢትዮጵያ አንድነት፣ በኢትዮጵያ ባንዲራ፣ በኢትዮጵያ ሙሉ ካርታ፣ ብሄራዊ ክብርናታሪክ ላይ በማይደራደሩ ድርጅቶች ላይ መዝመትና ክብረ-ወሰናቸውን ዝቅ ማድረግ የወያኔዎች ጸባይ ብቻ ሳይሆን ቋሚ ሥራቸው ነው።፡ ድሮም ሆነ ዛሬ ከወያኔዎችና ምንደኞች የምንጠብቀው ነገር ቢኖር ሌላ ቁምነገር ሳይሆን፣ ውሸት፣ ብልግና፣ ስድብ፣ የበታችነት ስሜትና የሞራል፣ የህሊናና የስነ-ልቦናና የማንነት ቀውስ ነው።፡ አወ በህይወት እንዳይኖር የምትመኙት ኢ ሕ አ ፓ ደግሞ ሲያምርኅ ይቀራል እንጂ ወያኔን ዕንቅልፍ ነስቶት ያለው አንድም የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው ሁለትም ኢ ሕ አ ፓ ብቻ ናቸው። ታዲያ አንተና ወያኔዎች እንደምትመኙት ኢ ሕ አ ፓ በህይወት ከሌለ፣ ሙቷልም ካላችሁለምን ሙት ወቃሽ ትሆናላችሁ? ከሌለ ምን ይኅን ሁሉ አስጨነቃችሁ? አስቀባጠራችሁ፤

አቶ ጌታቼው፣ ከስንት ጸሃፊዎችና ምሁሮች ጋር ማደጋችን በጀን እንጂ አንተ በምታሽጎደኡደው እጅግ በጣም ግድፈት በበዛበት ጽሁፍ ተደናቁረን በቀረን ነበር። አንድ ቁምነገር የሌለው፣ እርስ በራሱ የሚጠላለፍና የተሳከረ ጽሁፍን ጽሁፍ ሳይሆን ዝባዝንኬ እንለዋለን። በነገራችን ላይ ጥሩ ጽህፌ ማለት ሙቶ ቃላት ተጠቅሞ በአንድ ጊዜ ሙቶ መልዕክት ለአንባቢያን ማስተላለፍ መቻልን ይጠይቃል። እጂ እንዳንተ አንድ ሽኅ ቃላት አኀሮኅርጉሮ አንባቢውን confuse ማድረግ ማለት አይደለም። አቶ ጌታቼው ሌላው ጽሁፍህ በጣም ይጮሃል። በጣም ከመጮሁ የተነሳ ማስተላለፍ የሚገባውን ቁምነገር ሁሉ በግረመንገዱ ውጦት እንደሚቀር እቅጩን ልንገርህ። ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል ዕንዲሉ ስትጽፍ ምራቅህን ዋጥ አድርገኅ፣ ሰከንና ረጋ ባለ መንፈስ አወንታዊና ገንቢ በሆነ አቀራረብ ለመጻፍ ብትሞከር መከራከር፣ መወያየትና መረዳዳት እንችል ነበር ባይ ነኝ። በአንተ ቤት ከአንተ በላይ አዋቂ የለም ብለህ ስለምትገምት ሊገመግሙህ የሚችሉ ሰወች ሁሉ ከህሊናህ ውጭ ናቸው።፡ የመጣልህን ሁሉ መደፍደፍ እንጂ ማጣራትና እውነቱን ከውሸት፣ ጥሬውን ከልም፣ ጥሩውን ከመጥፎ ነገር ጨምቆ ማውጣት የሚባል ነገር እንደሌለህ የተበሳጨው በዕርህ ቋሚ ምሥክር ነው እልሃለሁ። እኔ በበኩሌ ከሰማይ በታች ያለን ነገር ሁሉ ጠላት ማድረግና ሙታንን በነቂስ መውቀስ የጤና አይመስለኝም።ማንነታቸውን የረሱ ሰዎች ራሳቸውን ስለረሱ ብቻ ዕነማን እንደሆኑ የሚያውቃቸው ሰው ያለ አይመስላቸውም በሚለው እስማማለሁ።

ያ ትዉልድ በተለይም ደግሞ በኢሕአፓ ጥላ ስር ተሰባስቦ የታገለው ክፍል የአግሩን እጣ ፋንታ በጋራ ለመወሰን ጎሳ፣ ሃይማኖትና ጾታ ሳይለየው በጋራ የሰራ ትውልድ ነው። ከጠባብብሔርተኞ፣ ተገንጣዮችና ትምክህተኞች ለየት ከሚያደርጉት ዋና ዋና ጸባዮቹ ዉስጥም ይህ በወርድ በስፋቱ፤ በቅርጽና ይዘቱ ሰፊና ኢትዮጵያዊ ሆኖ መቀጠሉ፣በኅሳና በቋንቋ ርዮት-አለም ከሰከሩት የጎሳ ጭቃ-ሹሞችና ተገንጣዮች ሁሉ ተለይቶና ተጻሮ በኢትዮጵያዊነቱ መፅናቱ፣ ጥላቻና ቁርሾ ትጥቅና ሥንቅቸው ከሆነው ትምክተኞችና ዘረኞች በሽታ ሁሉ በትግል ራሱን ያጸዳና እያጸዳ የቀጠለ ጨዋ ኢትዮጵያዊ ድርጅት መሆኑ ነው።